18.02.20011

# ሰላማዊ ሰልፍ በኦስሎ

በትላንትናው ዕለት በኢሕአፓ ኖርዌይ ክፍል አስተባባሪነት በኦስሎ ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ ተደርጓል። የሰልፉ ዓላማ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ በኖርዌይ መንግሥት እየተደረገ ያለውን አግባብ ያጣ ፍርድ ለመቃወም የተደረገ ሲሆን በሰላማዊ ሰልፉም የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ በኖርዌይና የእስልምናና የክርስትና የሐይማኖት ድርጅቶች በመገኘት ደጋፋቸውን ሰጥተዋል።

በዚህ ሰላማዊ ሰልፍ ኢትዮጵያውያን በጋራ ጩኸታቸውን ያሰሙበት፣ ተባብረው አንድ ሆነው ደምቀው የታዩበት ሰልፍ ነበር። በሰልፉም ወቅት በኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ለኖርዌይ ስደተኞች ሶሊዳሪቲ የተላከ መግለጫ በኦስሎ ተሰራጭቷል። የተለያዩ ሚዲያዎችም በስፍራው በመገኘት ዜናውን ዘግበዋል።

በዚህ ሰልፍ ለኖርዌይ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ የፍርድ ሚኒስትርና ለኖርዌይ ፓርላማ የተጻፈ ማመልከቻ ከኢሕአፓ ኖርዌይ ክፍል ተወክለው ለመጡ ኖርዌጅያን ባለሥልጣኖች በእጃቸው ተሰጥቷል።
ምክትል የፍርድ ሚኒስትሩም በንግግራቸው ላይ በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ እየከፋ መምጣቱን መገንዘባቸውን ለሰልፈኛው ገልጸው የስደተኛውንም ጥያቄ የሚታይበትንና ሁኔታው የሚመቻችበትን ሁኔታ ለመፍጠር መንግሥታቸው እየተነጋገረ መሆኑንም ጠቁመዋል፡ በመጨረሻም ሰልፉን ላዘጋጀውና ላስተባበረው የኢሕአፓ ኖርዌይ ክፍል ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

የሮድት ፓርቲ ምክትል መሪው በንግግራቸው የኖርዌይ መንግሥት የስደተኛውን ጉዳይ በአንክሮ እንዲመለከትና የፖለቲካ ተሳትፎ ያላቸው ግለሰቦች አገራቸው ቢላኩ የሚደርስባቸውን የከፋ አደጋ የኖርዌይ መንግሥት እንዲገነዘብና ሕይወታቸው አደጋ ላይ እንዳይወድቅ በማሳሰብ በኖርዌይ ብዙ ዓመት ያለፍቃድ ለኖሩ ስደተኞችና አኢትዮጵያውያን መኖሪያ ፍቃድ እንዲሰጣቸው አስገንዝበዋል።

የኖርዌይ ፓርላማ የህግ ቋሚ ኮሚቴው ተወካይ ለሰልፉ ደጋፋቸውን ሰጥተው ለመብት መታገል ጊዜ ሊወስድ ቢችልም በጽናት መታገል ለውጤት እንደምያበቃ ጠቁመዋል።

የኢሕአፓ ኖርዌይ ክፍልም በሰልፉ ላይ ተገኝተው ድጋፍ ለሰጡ ሁሉ ምስጋና በማቅረብ ወደፊትም ኢትዮጵያ ያዊው በአገሩ ጉዳይ ላይ ተባብሮ እንዲቆም አሳስቧል።